የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ የካቲት ፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.14
ADDIS ABABA 14th February, 2023

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፴/፪ሺ፲፭

የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩትን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.....ገጽ ፲፬፻ሺ፮፻፶፭

Content

Regulation No.530/2023

The Armauer Hansen Research Institute Establishment Regulation ……...Page 14655

ደንብ ቁጥር ፭፻፴/፪ሺ፲፭

የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፭፻ሺ፮፻፷፫/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፻፬ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአርማወር ሐንሰን የምርምር ኢንስቲትዩትን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፴/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ፡-

፩/ 'ምርምር' ማለት አዕምሯዊ እውቀትን በመጠቀም አዲስ ነገር ለማግኘት ዘዴን እና አሰራርን ለመፍጠር፣ ለመተንተን እና የምርምር ውጤትን ለማላመድ ወይም ለማሻሻል በቤተ-ሙከራም ሆነ ከቤተ-ሙከራ ውጭ የሚደረግ ተግባር ነው፣

Regulation Number 530/2023

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ARMAUER HANSEN RESEARCH INSTITUTE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 103 of Proclamation No. 1263/2021 enacted for the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Government of Ethiopia.

1. Short Title

This Regulation may be cited as the 'The Armauer Hansen Research Institute Establishment Regulation No.530/2023.

2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ 'Research' means an activity conducted in a laboratory and outside the laboratory by applying intellectual knowledge to discover, interpret and develop method and system and to adopt or improve finding;

፪/ ‘ምርምርና ልማት’ ማለት በፈጠራ እና በምርምር ስራ አዲስ ወይም የተሻሻለ ምርት እና አገልግሎትን ከፅንሰ-ሃሳብ ጀምሮ እስከ ገበያ ድረስ ያለውን ስራ የሚያካትት ነው፤

2/ ‘Research and development’ means work directed towards innovation and introduction of new or improved product and service, from concept to ultimately reaching the market;

፫/ ‘የህክምና ምርምር’ ማለት ቅድመ ክሊኒካል፣ ክሊኒካል እና ተሸጋጋሪ ምርምር በማካሄድ አዳዲስ ወይም የተሻሻለ ዕውቀትን ለማስገኘት የሚደረግ ምርምር ነው፡፡

3/ ‘Medical research’ means pre-clinical, clinical and translational research conducted to generate new and improved knowledge;

፬/ ‘ቅድመ-ክሊኒካል ምርምር’ ማለት ከህክምና ሙከራ በፊት የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ጤና-ነክ ምርምር ሆኖ ኢሚኒዮሎጂ፣ ማይክሮባዮሎጂ፣ ፓራሲቶሎጂ, ፋርማኮሎጂ፣ ቶክሲኮሎጂ፣ ባዮኢንፎርማቲክስ፣ ጄኔቲክስ፣ ሞለኪዩላር ባዮሎጂ፣ ኤትኖሜዲሲን/ ኤትኖቦታኒ፣ ፋይቶኬሚስትሪ፣ ፋርማሲዩቲካል ቴክኖሎጂ የመሳሰሉትን የሚያካትት በላቦራቶሪ ውስጥም ሆነ በላቦራቶሪ እንስሳት ላይ የሚደረግ ምርምር ነው፤

4/ ‘Pre-clinical research’ means any kind of health related research undertaken before clinical trial; which include but not limited to, immunology, microbiology parasitology, pharmacology, toxicology, bioinformatics, genetics, molecular biology, ethnomedicine/ethnobotany, phytochemistry, pharmaceutical technology, etc., conducted in laboratory (ex-vivo, in-vitro) and in laboratory animals (in-vivo);

፭/ ‘ክሊኒካል ምርምር’ ማለት ለሰው ጥቅም ለማዋል የታሰበ የመድኃኒት ፈዋሽነት፣ የመሳሪያ፣ የመመርመሪያ ምርትና የህክምና ዘዴ ደህንነትን እና ውጤታማነትን፣ ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርምር ነው። ይህም በሽታን ለመከላከል፣ ለህክምና፣ ለምርመራ ወይም የበሽታ ምልክትን ለማስታገስ ሊያገለግል ይችላል፤

5/ ‘Clinical research’ means a research that aims to determine the safety and effectiveness, efficacy of medication, device, diagnostic product and treatment regimen intended for human use. This may be used for prevention, treatment, diagnosis or for relieving symptom of a disease;

፮/ ‘ባዮሜዲካል ምርምር’ ማለት የህክምናውን ዘርፍ ዕውቀት ሊያሳድግ የሚችል ቅድመ ክሊኒካል ምርምር ሆኖ በውስጡም መሰረታዊ፣ ተግባራዊ፣ ኦፕሬሽናል እና ተሸጋጋሪ የሆነ ምርምርን የሚያቅፍ ነው፤

6/ ‘Biomedical research’ means pre-clinical research that includes basic, applied and translational research conducted to develop knowledge in the field of medicine;

፯/ ‘መሠረታዊ ምርምር’ ማለት የአንድን ነባራዊ ሁኔታ በጥልቀት ከመሰረቱ ለመረዳት እና አዳዲስ ዕውቀትን ለማስገኘት በተደራጀ ሁኔታ የሚከናወን ነው፤

7/ ‘Basic research’ means a systematic study and research directed towards greater knowledge or understanding of the fundamental aspects of phenomena.;

፰/ ‘ተግባራዊ ምርምር’ ማለት የጤና ችግርን በቀጥታ ለመፍታትና ምርምሩ ወደ ተግባር እንዲገባ የሚያስችል ሳይንሳዊ ምርምር ነው፤

8/ ‘Applied research’ means scientific research that can be directly applied to solve practical health problem;

፱/ ‘ተሸጋጋሪ ምርምር’ ማለት መሠረታዊ የሆነ የሳይንስ ምርምር ውጤትን በመውሰድ የጤና ችግርን ሊፈታ ወደሚችል ሳይንሳዊ ዘዴ ለማሸጋገር የሚያስችል የምርምር ዘዴ ነው፤

9/ ‘Translational research’ means a research that aims at making finding from basic science useful for practical application of science in solving practical problem that enhance human health and well-being;

፲/ ‘ኦፕሬሽናል ምርምር’ ማለት በሕክምና ወይም ጤና እንክብካቤ ሥራ አፈፃፀም ላይ ለውጤታማነት እንቅፋት የሆነ ችግርን ለመፍታት የሚደረግ ምርምር ነው፤

10/ ‘Operational research’ means a research that aims at solving problem in the implementation of medical or clinical care;

፲፩/ ‘ኤፒዲሚዮሎጂካዊ ምርምር’ ማለት በተወሰነ ህብረተሰብ ውስጥ ያለ የበሽታን ስርጭት እና የጤናን ሁኔታ የሚወስን ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ምርምር ነው፤

11/ ‘Epidemiological research’ means a research that analyzes the distribution, pattern and determinant of health and disease condition in defined population;

፲፪/ ‘የህክምና ሙከራ’ ማለት የመድኃኒት ወይም የህክምና ሂደት ላይ ትክክለኛ መረጃን በሳይንሳዊ መንገድ ለማግኘት ቁጥጥር የሚደረግበት ሆኖ በሰው ላይ የሚሞከር የምርምር ፍተሻ ነው፤

12/ ‘Clinical Trial’ means testing medicine or medical procedure on human through controlled experiment intended to yield scientifically valid information on the effect of intervention on health-related biomedical or behavioral outcome;

፲፫/ ‘የተቀናጀ የጤና ምርምር’ ማለት በሰው፣ በእንስሳት እና በአካባቢያቸው መካከል ያለውን ትስስር የበለጠ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በአገር አቀፍ ደረጃ ቅድሚያ በተሰጠው ከእንስሳት ወደሰው በሚተላለፍ በሽታ ላይ በተያያዘ እና ሁሉን አቀፍ በሆነ መንገድ የሚያጠና ምርምር ነው፤

13/ ‘One Health Research’ means a research that investigates on national prioritized zoonotic disease in an integrated and holistic manner to provide a more comprehensive understanding of the linkage between human, animal, and their shared environments;

፲፬/ ‘የሕክምና ባዮቴክኖሎጂ ምርምር’ ማለት የስነ-ህይወት ነባራዊ ሂደትን እና ህዋስን ወይም የእነዚህን ተዋጽኦ በመጠቀም ጠቃሚ ምርትን በማዳበር ወይም ተገቢ እውቀት በማመንጨት የህብረተሰቡን ጤና እንክብካቤ፣ ህክምና እና ደህንነትን ሊያሻሽል የሚችል ምርምር ነው፤

14/ ‘Medical biotechnology research’ means the use of living system and organism or derivative to develop useful product or generate relevant knowledge that can improve clinical care, health and well-being of the public;

፲፭/ ‘ባዮኢንፎርማቲክስ’ ማለት የህብረተሰብን ጤና ለማሻሻል የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ባዮሎጂካል መረጃዎችን የማከማቸት፣ የማደራጀት እና የመተንተን ሳይንሳዊ ዘዴ ነው፤

15/ ‘Bioinformatics’ means a scientific method of storing, organizing and analyzing biological information using computer technology to improve the well-being of the public;

፲፮/ ‘የባዮኢኪዩቫለንስ ጥናት’ ማለት ሁለት ተመሳሳይ መድኃኒቶች ወይም አንድ ዓይነት መድኃኒት ሆነው በሁለት ዓይነት ዝግጅቶች የቀረቡ መድኃኒቶችን በደም ውስጥ የሚገኙበትን መጠን ተመሳሳይነት በንፅፅር የሚያጠና የተለየ የጥናት ዘዴ ነው፤

16/ ‘Bioequivalence study’ means a special type of study, where two drugs or two sets of formulation of the same drug are compared to show that they have nearly equal bioavailability parameters;

፲፯/ ‘መድኃኒት’ ማለት የሰውን በሽታ፣ የተዛባ ወይም ጤነኛ ያልሆነ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ሁኔታ ወይም ተያያዥ ምልክቶችን ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል፣ የሰውን አካላዊ ወይም አዕምሯዊ አሰራር በጠቃሚ መልኩ ለማስተካከል፣ ወደ ነበረበት ለመመለስ ወይም ለማሻሻል፣ ወይም ከምግብ በስተቀር የሰውነትን መዋቅር ወይም ማንኛውንም የሰውነትን ተፈጥሯዊ ተግባር በጠቃሚ መልኩ ለመለወጥ የሚውል ማንኛውም ንጥረ-ነገር ወይም የንጥረ-ነገሮች ውህድ ሆኖ ለነዚህ ምርቶች ጥሬ ዕቃነት የሚውል ማንኛውንም ንጥረ-ነገርን ያጠቃልላል፤

17/ ‘Medicine’ means any substance or mixture of substance used in the diagnosis, treatment, mitigation or prevention of human disease, disorder, abnormal physical or mental state, or the symptoms thereof; used in restoring, correcting or beneficial modification of organic or mental functions in human; or articles other than food, intended to affect the structure or any function of the body of human and it includes articles intended for use as a component of any of the above specified articles;

፲፰/ ’የባህል ሕክምና’ ማለት የእንስሳት ተዋፅያን፣ እፅዋትን፣ ማዕድንን በመጠቀም መንፈሳዊ ሕክምናን፣ የሙያዊ ቴክኒክን እና ልምምድን በተናጠል ወይም በማጣመር ጤናን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመመርመር እና ለመከላከል የምንጠቀምበት ማንኛውም የጤና አሠራር፣ ዘዴ፣ ዕውቀትና እምነት ነው፤

18/ ‘Traditional medicine’ means any health practice, method, knowledge, and belief which involve the medicinal use of animal, plant and mineral, spiritual therapy, manual technique and practice either separately or in combination to care for, diagnose, prevent disease or maintain health;

፲፱/ ‘የህክምና መሣርያ’ ማለት የሚፈለገውን ተግባር ፋርማኮሎጂካል፣ ኢሚውኖሎጂካል ወይም ሜታቦሊክ ዘዴ በመጠቀም በቀጥታ የማያከናውን ማንኛውንም መገልገያ፣ ቅንብረ-መሣሪያ፣ መተግበሪያ፣ ማሽን፣ አፕሊያንስ፣ ሰውነት ውስጥ የሚቀመጥ ነገር፣ ናሙናን ከሰውነት ውጭ ለመመርመር የሚረዳ ውህድ ወይም የልኬት ማረጋገጫ፣ ሶፍትዌር፣ ዕቃ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቁስ ሆኖ በአምራቹ ድርጅት ለብቻው ወይም በመቀላቀል ለሰው ህክምና ጥቅም ላይ እንዲውል የተዘጋጀ መሣሪያ ሲሆን ተያያዥ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ወይም እርግዝናን ለመከላከል የሚረዳ መሣሪያን ያጠቃልላል፤

19/ ‘Medical device’ means any instrument, apparatus, implement, machine, appliance, implant, reagent for *in vitro* use, software, material or other similar or related articles and their accessories, which does not achieve its primary intended action by pharmacological, immunological or metabolic means, in or on the human body, and intended by the manufacturer to be used, alone or in combination, for medical purpose and includes device intended for related medical use and control of contraception.;

፳/ ‘ፋርማሲዩቲካል’ ማለት ማንኛውም ምርት፣ ውህድ፣ ዘመናዊና ባህላዊ መድኃኒት፣ ክትባት ወይም ቴራፒዩቲክ ምርት፣ መድኃኒትነት ያለው ምግብ፣ የህክምና መሳሪያ፣ የግልና የጤና መጠበቂያ ምርት ሆኖ ለሰው ልጅ ጥቅም የሚውልና ህጋዊ ቁጥጥር የሚደረግበት ነው፤

20/ ‘Pharmaceutical’ means any product, compound, conventional and traditional medicine, vaccine or therapeutic product, nutraceutical, medical device, personal and healthcare product, which is subject to regulation for human use;

፳፩/ ‘መድኃኒትነት ያለው ምግብ’ ማለት ማንኛውም ምግብ ወይም የምግብ አካል የሆነ እና በሽታን መከላከልና ማከምን ጨምሮ የህክምና ወይም የጤና ጥቅም የሚሰጥ ማንኛውም ንጥረ-ነገር ነው፤

21/ ‘Nutraceutical’ means any substance that is a food or part of a food and provides medical or health benefit, including the prevention and treatment of disease;

፳፪/ ‘ኢንዱስትሪ’ ማለት የክትባት፣ የመመርመሪያ ዘዴ፣ ቴራፒዮቲክስ፣ የዘመናዊ እና ባህላዊ መድኃኒት፣ መድኃኒትነት ያለው ምግብ፣ ሌላ የፋርማሲዩቲካል ምርት፣ የህክምና መሳሪያን ወይም የግል እና የጤና መጠበቂያ ምርትን በተናጠል ወይም በጥምረት በማምረት ላይ የተሰማራ ድርጅት ነው፤

22/ ‘Industry’ means a facility engaged in manufacturing vaccine, diagnostic, therapeutics, modern and traditional medicine, nutraceutical, other pharmaceutical product, medical device or personal and health care product, separately or any combination of these items;

፳፫/ ’የግል እና የጤና መጠበቂያ ምርት’ ማለት በሰውነት የተፈጥሮ ቅርጽ ወይም ተግባራት ላይ ተፅዕኖ ሳያሳድር በሰው አካል ላይ በማድረግ፤ ለማፅዳትና ለማስዋብ የሚጠቅም ማንኛውም ዓይነት ምርት ነው።

23/ ‘Personal and health care product’ means any preparation intended to be applied to the human body for cleansing and beautifying the appearance without affecting the body's structure or function;

፳፬/ ’ማምረት’ ማለት የክትባት፣ የመመርመሪያ ዘዴ፣ ቴራፒዮቲክስ፣ የባህላዊ መድኃኒት፣ መድኃኒትነት ያለው ምግብ እና ሌላ የፋርማሲዩቲካል ምርት ማምረቻ ሂደት ውስጥ ከአክቲቭ ንጥረ-ነገር ዝግጅት እስከ ቅመራ እና/ወይም ማሸጊያ ድረስ ያለውን ማንኛውንም ደረጃ ያካትታል፤

24/ ‘Production’ means any stage of medicine, vaccine, diagnostic, therapeutics, nutraceutical and other pharmaceutical product manufacturing process from production of active pharmaceutical active ingredient to formulation and/or packaging;

፳፭/ ’የቴክኖሎጂ ሽግግር’ ማለት ከኢንዱስትሪ፣ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከመንግስት እና ከሌሎች የምርምር ተቋማት ክህሎትን፣ ቴክኖሎጂን፣ ዳታን፣ ንድፍን፣ ፈጠራን፣ ቁስን፣ ሶፍትዌርን፣ ቴክኒካል እውቀትን፣ የንግድ ሚስጥርን፣ የማምረቻ ዘዴን እና መሳሪያን የማስተላለፍ ሂደት ሆኖ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ እድገትን ለብዙሃን ተጠቃሚዎች ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና የህብረተሰብ ጤናን ለማሻሻል የሚረዳ ቴክኖሎጂን ወደ አዲስ ምርት፣ ሂደት፣ መተግበሪያ ቁስ ወይም አገልግሎቶች ማዳበር እና መጠቀም ነው፡

25/ ‘Technology transfer’ means the process of sharing of skill, technologyy, data, design, invention, material, software, technical knowledge, trade secret, method of manufacturing device and equipment among manufacturing industry, universities, government and other research institution to ensure scientific and technological development is accessible to a wider range of user who can then develop and exploit the technology into new product, process, application, material or service applicable to improve public health;

፳፮/ ‘ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር’ ማለት እንደየቅደም ተከተላቸው የጤና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

26/ ‘Ministry’ or ‘Minister’ means the Ministry of Health or Minister, respectively;

፳፯/ ‘ክልል’ ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን፥ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፳፰/ ‘ሰው’ ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያጠቃልላል፡፡

27/ ‘Region’ means any region constituted as per Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

28/ 'Person' means any physical or juridical person;

29/ Any expression in the masculine gender includes the feminine gender.

፫. ስለመቋቋም

የአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ ’ኢንስቲትዩት እየተባለ የሚጠራ’) የህግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

3. Establishment

The Armauer Hansen Research Institute (hereinafter ‘the Institute’) is here by establish by this Regulation an autonomous Federal Government Office having its own legal personality.

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

4. Head Office

The Institute shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices as may be necessary.

፭. የኢንስቲትዩቱ ዓላማ

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ለጤና እና ለሥነ-ምግብ ችግሮች ቅድሚያ በመስጠት ሀገራዊ የጤና ምርምር አጀንዳ ላይ የተመሰረተ ተላላፊ እና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ ምርምር ማካሄድ እና ሳይንሳዊ እና ቴክኖሎጂያዊ እውቀቶችን በመጠቀም የህብረተሰቡን ጤና ማሻሻል፤

፪/ የጤና ፈጠራዎችን ማሳደግ እና በባህላዊና ዘመናዊ መድኃኒቶች፣ በክትባቶች፣ በመመርመሪያ እና ቴራፒዩቲክስ ዘዴዎችና ስልቶች ላይ ምርምር ማድረግ፤

፫/ ጥራታቸውን የጠበቁ የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የጤና መጠበቂያ ምርቶች አቅርቦትን ማጠናከርና ማሳደግ፤

5. Objective of the Institute

The Institute shall have the following objectives:

1/ Undertake research, based on the national health research agenda, on priority to health and nutrition problems related with communicable and non-communicable diseases, and thereby applying scientific and technological knowledge to improve health and well-being of the public;

2/ Promote health innovations and undertake research on traditional medicines, vaccines, diagnostics and therapeutic tools and strategies;

3/ Promote and strengthen local production of pharmaceutical manufacturing industry products to improve access to healthcare products through quality production;

፬/ በጤና ምርምር እና ልማት የእውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል ሆኖ ማገልገል፤

፭/ የህክምና ሙከራዎችን እና የባዮኢኪዩቫለንስ ጥናት ማካሄድ፤ እና

፮/ በጤና ምርምርና ልማት ዘርፍ ሀገራዊ የሰው አቅምን መገንባት እና በውድድር የሚገኙ የምርምር ስራ ማስኬጃ ገንዘብ ማስገኘት፡፡

4/ Serve as a hub for knowledge and technology transfer in health research and development ;

5/ Conduct clinical trials and bioequivalence studies; and

6/ Build national human capacity in health research and development and secure competitive research grants

፮. <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉትን የማድረግ ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

6. <u>Powers and Duties of the Institute</u>

The Institute shall have the powers and duties to:

፩/ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሚኒስቴሩ ቅድሚያ በሚሰጣቸዉ የምርምር አካባቢዎች መሠረት በተላላፊ እና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ በመሠረታዊ፣ ተግባራዊ፣ የሕክምና፣ ቅድመ-ክሊኒካል፣ ክሊኒካል፣ ተሸጋጋሪ፣ ኦፕሬሽናል፣ ኤፒዲሚዮሎጂካዊ፣ የተቀናጀ የጤና ምርምር፣ በሕክምና ባዮቴክኖሎጂ፣ በባህላዊ ሕክምናና በሕክምና ልምዶች ላይ ምርምር ያደርጋል፤

1/ Conduct basic, applied, medical, preclinical, clinical, translational, operational, epidemiological research on communicable and non-communicable diseases, one health research, medical biotechnology, traditional medicine and medical practices based on the ministries national research priority areas;

፪/ ሥር በሰደዱ በሽታዎች እና በተዛማች የጤና ችግሮች ለተጠቁ በሽተኞች የመከላከል፣ የመመርመር እና የአመጋገብ ለውጦቻቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል የክሊኒካል ሥነ-ምግብ እና መድኃኒትነት ያላቸው የምግብ ምርቶች ላይ ምርምር ያካሂዳል፣ መድኃኒትነት ያላቸው የምግብ ምርቶችን የማልማት፣ የማበልጸግ፣ እና የመገምገም ስራ ያካሂዳል፤

2/ Conduct research on clinical nutrition and nutraceuticals for the prevention, diagnosis, and management of nutritional changes in patients linked to chronic diseases and related conditions, primarily in health care; conduct product development, fortification and evaluation of nutraceuticals;

፫/ የዕውቀት አስተዳደርን ያጠናክራል፤ የምርምር ግኝቶችን እና ሌሎች መረጃዎችን በህትመት እና በሌሎች መንገዶች ያሰራጫል፤

3/ Strengthen Knowledge management; data synthesis and utilization, dissemination of research findings through publication and other means;

፬/ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት በምርምር ግኝቶች ላይ በመመስረት ለሚመለከታቸው አካላት የፖሊሲ አጭር መግለጫዎችን ያቀርባል፤የመድኃኒት ፍለጋ ሂደትን ለማገዝ እና ለማፋጠን የኢትዮጵያን ባህላዊ (የእፀዋት) መድኃኒት መረጃ ማከማቻ ማቋቋም እና የባዮኢንፎርማቲክስ ጥናቶችን ያካሂዳል፤

4/ Submit policy briefs to concerned bodies based on the research findings for evidence-based decision making; establish Ethiopian Traditional Medicine data repository and undertake bioinformatics studies so as to aid and hasten the drug discovery process;

ሸ/ ለክትባት፣ የመመርመሪያ ዘዴዎች፣ ቴራፒዩቲክስ፣ የባህላዊ መድኃኒት እና ሌሎች ፋርማሲዩቲካል ምርቶች ልማት የሚውሉ ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎችን በመለየት ወደ አምራቾች ያስተላልፋል፤

5/ Identify and transfer relevant technologies applicable to the development of vaccine, diagnostics, therapeutics, traditional medicine and other pharmaceutical product to manufacturers;

ቀ/ አዲስ ወይም የተሻሻሉ የክትባት፣የመመርመሪያ ዘዴዎች ፣ ቴራፒዩቲክስ ፣ የባህላዊ መድኃኒት እና ሌሎች የፋርማሲዩቲካል ምርቶች አልጎሪዝምን (ስልተ-ቀመር) እና ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎችን ያዳብራል፤

6/ Develop new or improved diagnostics, vaccines, therapeutics, traditional medicine, and other pharmaceuticals, algorithms and relevant technologies;

በ/ የክትባት፣ የመመርመሪያ ዘዴዎች፣ ቴራፒዩቲክስ፣ የባህላዊ መድኃኒት እና ሌሎች የፋርማሲዩቲካል ምርቶችን በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚያበረታቱ እና የሚያጠናክሩ ስልቶችን እና የድርጊት መርሃ ግብሮችን ያወጣል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

7/ Formulate strategies and action plans that promote and strengthen local production of vaccines, diagnostics, therapeutics, traditional medicine, and other pharmaceuticals and implement the action plans;

ተ/ ምርት ማልማትና የማምረት ተግባራትን ያከናውናል፤ የወጡትንም ቴክኖሎጂዎች ወደ ኢንዱስትሪው በማሸጋገር ወደ ገበያ እንዲገቡ እና ኢንዱስትሪው የምርምር እና ልማት ክፍሎችን እንዲያቋቁሙ ይደግፋል፤

8/ Perform product development activities and production; transfer these technologies to the industry, support them enter the market and establish research and development units;

ቸ/ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ የሚያስችሉ ፕሮቶታይፕ ማበልፀጊያ፣ ፓይለት ፕላንት እና ላቦራቶሪዎችን ያቋቁማል፤

9/ Establish pilot plants and laboratories to develop prototype and support the industry ;

ኀ/ የህክምና ሙከራ ፍላጎቶችን እና ቦታዎችን ይለያል፤ የህክምና ሙከራዎችን ያካሂዳል፤ ያጠናክራል፤

10 Identify clinical trial sites; conduct and strengthen clinical trials;

ነ/ የመድኃኒት ግኝት ሂደትን ለማገዝ እና ለማፋጠን የኢትዮጵያን ባህላዊ መድኃኒት መረጃ ቋት ያቋቁማል እንዲሁም የባዮኢንፎርማቲክስ ጥናቶችን ያካሂዳል፤

11/ Establish Ethiopian traditional medicine data repository and undertake bioinformatics studies so as to aid and hasten the drug discovery process;

ኘ/ በከፍተኛ ደረጃ በሽታ አምጪ የሆኑ ተህዋስያን ላይ ክትባቶችን እና ቴራፒዩቲክስ ላይ የሚደረገውን ምርምርን እና ልማትን ለማገዝ እስከ ደረጃ አራት ላቦራቶሪ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤

12/ Establish and administer up to level four laboratory to facilitate vaccine and therapeutic research and development of highly pathogenic organisms;

ኸ/ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች እና የባህል ህክምና ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ለመድኃኒታማ ዕፅዋትና ለሀገር-በቀል እውቀቶች ከለላና ጥበቃ ያደርጋል፤ ሰነዶች ያደራጃል፤ ጥቅም ላይ ያውላል፤ ወደ ገበያ እንዲገቡ ያደርጋል፤

13/ Collaborate with concerned organizations and traditional medicine practitioners for the conservation, protection, documentation, utilization and commercialization of medicinal plants and indigenous knowledge;

፲፬/ የባዮኢኪዩቫለንስ ምርምር ያካሂዳል፤ ለፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ባዮኢኪዩቫለንስ ማምጣማ ድጋፍ እና አገልግሎት ይሰጣል፤ ለህክምና ሙከራዎች እና ባዮኢኪዩቫለንስ ምርምር እንደ ኮንትራት ምርምር ተቋም ሆኖ ያገለግላል፤

14/ Conduct Bioequivalence research; provide support and service in bio-equivalence assessment for pharmaceutical industry; and serve as Contractual Research Organization (CRO) for clinical trials and Bioequivalence research;

፲፭/ የክትባት፣ የመመርመሪያ ዘዴዎች፣ ቴራፒዩቲክስ፣ የባህላዊ መድኃኒት፣ መድኃኒትነት ያላቸው ምግቦች እና ሌሎች የፋርማሲዩቲካል ምርቶች ልማትን የሚደግፉ የገበያ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ ስራን ከሚመለከታቸው ተቋማትና ድርጅቶች ጋር በትብብር ይሰራል፤ በአምራች ኢንዱስትሪ ውስጥ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚረዱ የፕሮጀክት መግለጫዎችን ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፤ የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም፣ አተገባበርና ድህረ-ትግበራን ይከታተላል፤

15/ Conduct market studies and assist investment promotion that support the development of diagnostics, vaccines, therapeutics, traditional medicine, nutraceuticals and other pharmaceuticals in collaboration with relevant institutions and organizations; prepare and disseminate project profiles that may be helpful in expanding investment in manufacturing industry; follow up projects during implementation, operation, and post operation phases;

፲፮/ ለባህላዊ ሕክምና ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች በባህላዊ ሕክምና ላይ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤

16/ Provide capacity building assistance to traditional medicine practitioners and researchers;

፲፯/ ለፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ አምራች ዘርፍ ማህበራት፣ ለህክምና፣ ለባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች እና ሌሎች ተዛማጅ የሙያ ማህበራት በጤናው ዘርፍ እድገት ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ድጋፍ ያደርጋል፤

17/ Provide support to pharmaceutical manufacturing sectorial associations and medical, traditional medicine practitioners and other related professional associations so that they play their proper role in the development of the health sector;

፲፰/ በጤና ምርምር መስክ የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ተመራማሪዎች ሽልማት ይሰጣል፤

18/ Award researchers who have got outstanding results in the field of health research;

፲፱/ በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሠረት በተመረጡ የህክምና ምርመራ ዘዴዎች፣ የስልጠና፣ የማማከር እና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው የክፍያ ተመን መሰረት ለሚሰጠው አገልግሎቶች ክፍያ ያስከፍላል፤

19/ Provide service on selected diagnostics, training, consultancy and other services upon request and charge fees for the services it renders in accordance with the rate stipulated under regulation issued by the Council of Ministers;

፳/ የሕክምና ተመራማሪዎች የምርምር ውጤቶችን ለመገምገምና የጤና እንክብካቤንና ህክምናን ለማሻሻል ፣ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ እና ተጨማሪ የምርምር ፍላጎቶችን ለመለየትና ለመወሰን የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤

20/ Conduct activities that would help to review research outputs and determine validity to improve clinical care and identify further research needs for medical researchers;

፳፩/ በቅድመ-አዋጭነትና በአዋጭነት ጥናት፣ በምርት ሂደት፣ በምርት እቅድ ዝግጅትና በዘርፉ የጥራት ማረጋገጫ ላይ ለኢንዱስትሪው የቴክኒክ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤ በተጨማሪም በመሠረታዊ፣ በተግባራዊ፣ በሕክምና፣ በቅድመ-ክሊኒካል፣ በክሊኒካል፣ በተሸጋጋሪ፣ በኦፕሬሽናል፣ በኤፒዲሚዮሎጂካል፣ በሕክምና ባዮቴክኖሎጂ፣ በባህላዊ ሕክምና ምርምር ላይ ለሌሎች ተቋማት ድጋፍና የማማከር አገልግሎት ይሰጣል፤

21/Provide technical support and consultancy service to the Industry on pre-feasibility and feasibility study, production process, production planning and quality assurance to the sector; further support and consult on basic, applied, medical, preclinical, clinical, translational, operational, epidemiological, medical biotechnology, traditional medicine research to other institutions;

፳፪/ የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን እንዲጠቀሙ እና በአነስተኛ አሉታዊ አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ተፅእኖ ውስጥ እንዲሰሩ ድጋፍ ይሰጣል፤

22/ Provide support to pharmaceutical Industry to use renewable energy sources and operate in a reduced negative environmental and social impact;

፳፫/ ለአምራች ኢንዱስትሪ የመልካም አመራረት ሥርዓት ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ድጋፍ በማድረግ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ ይሰጣል፤

23/ Provide support to the manufacturing Industry to get good manufacturing practice certification so as to make them competitive at national and international market;

፳፬/ በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች እና የፈጠራ ባለቤትነት ማረጋገጫዎች ለማግኘት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፤ በኢንስቲትዩቱ ለተዘጋጁ ተቋማዊ የምርምር መረጃዎች፣ ግኝቶች እና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥበቃም በመተባበር ይሰራል፤

24/ Work in collaboration with concerned authorities to obtain intellectual property rights and patents at national and international level, and to ensure security of research data, findings and technology outputs developed by the Institute;

፳፭/ ከአገር አቀፍና ከዓለም አቀፍ አጋሮች ጋር ትስስር በመፍጠር ጥራት ያለው የጤና ምርምርን ለማጠናከር፣ የቴክኒክ ድጋፍን ለማረጋገጥ፣ ብቃትን ለማሳደግና የገቢ ምንጮችን ለመጠቀም፣ የቴክኖሎጂ፣ የእውቀት ሽግግርና የጋራ ተጠቃሚነትን ያሳድጋል፤ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በቴክኖሎጂ እና ቴክኒካል ድጋፎች፣ ተግባራዊ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት እና በማካሄድ ለኢንዱስትሪ ልማት እና ተወዳዳሪነት ይሰራል፤

25/ Foster networking with national and international partners to strengthen the conduct of quality health research, secure technical support, develop competence and leverage funds, boost technology and knowledge transfer and mutual benefits; work in collaboration with other stakeholders, prepare and conduct practical training on technology and technical matters that may assist the development and competitiveness in the Industry;

፳፮/ ከአገር አቀፍና ከዓለም አቀፍ ዩኒቨርሲቲዎች እና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በሰው ኃይል ልማት በክትባቶች፣ በመመርመሪያ ዘዴዎች፣ በቴራፒዩቲክስ፣

26/ Cooperate with national and international universities and relevant institutions to advance the national capacity in human resource development on diagnostics,

በባህላዊና ዘመናዊ መድኃኒቶች፤ መድኃኒትነት ባላቸው ምግቦች እና በሌሎች ፋርማሲዩቲካል ምርምርና ልማት እና የማኑፋክቸሪንግ ስራዎች ላይ ያለውን አገራዊ አቅም ያሳድጋል፤

vaccines, therapeutics, nutraceuticals and other pharmaceutical research and development and manufacturing activity;

፳፯/ በኢንስቲትዩቱ የምርምር ስራዎች፣ የምርምር ተሳታፊዎችን እና ሌሎችንም ለመጠበቅ የወጡ የአገራዊ እና ዓለም አቀፍ የምርምር ሥነ-ምግባር መመሪያዎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

27/ Ensure the Institute's research work comply to the national and international research ethics guidelines to protect research participants and others;

፳፰/ አዳዲስ የምርምር ሀሳቦችን በመለየት እና በመደገፍ ሀገራዊ የጤና ፈጠራዎችን ያሳድጋል፤

28/ Promote national health innovations through identifying and supporting innovative ideas;

፳፱/ ከአገር አቀፍ እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር የጋራ የጤና ምርምር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጋራ ምርምር ለማድረግ ለሌሎች አካላት ድጋፍ ይሰጣል፤

29/ Undertake joint health research in collaboration with national and international institutes; provide support to other organs to undertake a joint research as deemed necessary;

፴/ ከአገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች በውድድር የሚገኘውን የምርምር ስራ ማስኬጃ ገንዘብ ያስተዳድራል፤

30/ Administer competitive research grants from national and international sources;

፴፩/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፤ይከሰሳል፡፡

31/ Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name.

፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

7. <u>Organization of the Institute</u>

The Institute shall have:

፩/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ዋና ዳይሬክተር

1/ A Director General appointed by the Prime Minister;

፪/ እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤

2/ Deputy Director Generals as deemed necessary;

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች፤ እና

3/ The necessary staff; and

፬/ የሳይንሳዊ አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ 'ቦርድ' እየተባለ የሚጠራው)፤

4/ Scientific Advisory Board (hereinafter called the 'Board').

ይኖሩታል፡፡

፰. <u>የቦርድ አባላት</u>

8. <u>Members of the Board</u>

፩/ የቦርድ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በኢንስቲትዩቱ አቅራቢነት በሚኒስትሩ ይሰየማሉ፡፡

1/ Members of the Board, including the chairperson, shall be presented by the Institute and appointed by the Minister.

፪/ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ነው።

2/ The Board shall be responsible to the Ministry.

፫/ የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ፭ ዓመት ሲሆን የቦርዱ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም።

3/ The term of service of the Board members shall be 5 years and may not be elected for more than two terms.

፱. የቦርዱ ተግባራት እና ኃላፊነት

9. Duties and Responsibilities of the Board

ቦርዱ፡-

The Board:

፩/ በምርምር ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ሌሎች አንኳር ተቋማዊ ጉዳዮች ላይ በማማከር፣ ኢንስቲትዩቱን በህክምና ምርምር በቴክኖሎጂና ፈጠራ ላይ ተወዳዳሪና ዘላቂ እድገት ለማበርከት እንዲችል ድጋፍ ይሰጣል፤

1/ Support the Institute to foster its competitiveness and sustainable growth in technology and innovation by advising the Institute in research policy, strategy and other fundamental issues of the Institute;

፪/ ኢንስቲትዩቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን፣ ልዩ ልዩ፣ ዘመናዊና ችግር-ፈቺ የሆኑ ሳይንሳዊ የአሰራር ስልቶች እንዲዘረጉ ያማክራል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

2/ Advise and support the Institute to devise advanced and problem-solving scientific methodologies to ensure its global competitiveness;

፫/ ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች አቻ ተቋማትና የልማት አጋሮች ጋር ትስስር እንዲፈጥርና ተቋማዊ እድገትን እንዲያመጣ ያግዛል፣ እንዲሁም አህጉራዊ እና ዓለምአቀፋዊ በሆኑ የህክምና ምርምርና ልማት ስራዎች እንዲሳተፍና በትብብር እንዲሰራ ድጋፍ ያደርጋል፤

3/ Support the Institute to create collaboration with similar institutes and partners; participate in national and international health research development works and engage in cooperative works;

፬/ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያሳያል፤

4/ Evaluate the Institute’s annual report and give advisory directions.

፲. የቦርዱ ስብሰባዎች

10. Meeting of the Board

፩/ ቦርዱ እንደአስፈላጊነቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል፡፡

1/ The Board shall meet regularly or as frequent as its function requires.

፪/ ከቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በስብሰባ ከተገኙበት ምልዓተ ጉባኤ ይኖራል፡፡

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Board are present at a meeting.

፫/ የቦርዱ ማጠቃለያ ሀሳብ በስምምነት ወይም በድምፅ ብልጫ ያልፋል፣ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

3/ The Board shall draw conclusions by consensus or a majority vote and, in the case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ሥነ ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል።

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may adopt its own rules of procedure.

፲፩. <u>የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን ኢንስቲትዩቱን ይመራል፣ ያስተዳድራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከተውን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱ የስራ እንቅስቃሴና በጀት ዕቅድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ሲፀድቅም ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ኃላፊነቱ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይም በየደረጃው ላሉ ለሌሎች ኃላፊዎች ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፲፪. <u>የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የተመደበበትን የዘርፍ ተግባራት ያከናወናል፤ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

11. <u>Powers and Duties of the Director General</u>

1/ The Director General, shall be the chief executive officer of the Institute and shall, direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer the employees of the Institute in accordance with the Federal Civil Service Laws;

c) cause the preparation of activity plans and budgets of the Institute and ensure the implementation of the same upon approval ;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate some of his powers and responsibilities to the Deputy Director General or to other officials at all levels for the efficiency of the Institute.

12. <u>Powers and Duties of the Deputy Director General</u>

The Deputy Director General shall:

1/ Execute wing activities he is assigned on; execute other responsibilities that is given by the Director General;

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፣ ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ካሉና ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለዉ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶት ይሠራል።

2/ Represent the Director General in his absence, when there are more than one Deputy Director Generals and the Director General has not given special delegation, the Deputy Director who comes first in terms of appointment shall represent the Director General.

፲፫. በጀትና የገቢ ምንጭ

የኢንስቲትዩቱ በጀትና የገቢ ምንጭ፡-

፩/ ከመንግስት በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚመደብ በጀት፣

፪/ ከውስጥ ገቢ የሚገኝ፣ እና

፫/ ከአገር ውስጥ እና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች በውድድር ወይም በስጦታ የሚገኙ የምርምር ስራ ማስኬጃ ገንዘብ።

13. Budget and Sources of Income

The Budget and sources of income of the Institute shall be from:

1/ The Budget allocated by the government in cash or in kind;

2/ The income generated internally; and

3/ The competitive or gratuitous research grants from local and international organizations.

፲፬. የሂሳብ መዛግብት ስለመያዝ

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይኖሩታል።

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግባት እና ገንዘብ-ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።

14. Books of Accounts

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or by an Auditor designated by him.

፲፭. የተሻሩ ደንቦች እና የማይተገበሩ ሕጎች

የአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፸፮/፪ሺ፰ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

15. Repealed Regulations and Inapplicable Laws

The Armauer Hansen Research Institute Establishment Council of Ministers Regulation No. 376/2016 is here by repealed.

፲፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ቀን የካቲት ፯ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

አብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር

16. Effective Date

This Regulation shall enter in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, on this 14th day of February, 2023

ABIY AHMED (DR)

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA